GSMA

# የስልክ በይነመረብ ክህሎቶች የሥልጠና መርጃ ስብስብ

## ሰዎችን መደበኛ የስልክ በይነመረብ ክህሎቶችን ለማስተማር የተዘጋጀ መመሪያ



የቅጂ መብት © 2024 GSM Association

# ሞጁል 13፦ የተደራሽነት ባህሪያት

## የስልክ በይነመረብ ክህሎቶች የሥልጠና መርጃ ስብስብ

ሰዎችን መደበኛ የስልክ በይነመረብ ክህሎቶችን ለማስተማር የተዘጋጀ መመሪያ

# እይታቸው አነስተኛ ለሆነ ወይም አይነ ስውራን ለሆኑ ሰዎች የተደራሽነት ባህሪዎች

## ይህ ምንድን ነው?

**ያብራሩ፦** «ዝቅተኛ የማየት ችሎታ ያላቸው ወይም ምንም ማየት የማይችሉ አንዳንድ ሰዎች በማያ ገጹ ላይ ያለውን ነገር ማየት ሊያዳግታቸው ይችላል። በስልኩ ላይ እነሱን ሊረዱ የሚችሉ ባህሪያት አሉ። ለፍላጎታቸው ተስማሚ የሆኑ የተለያዩ አማራጮችን ማሳየት አለብን። አብዛኛውን ጊዜ ሰዎች እነዚህን ባህሪያት በማጣመር ይጠቀማሉ።»

## የሚያስፈልጉዎ ቁሳቁሶች፦



Android ስልክ




የተደራሽነት
ባህሪያት ፖስተሮች

## ለምን ሊጠቀሙበት ይችላሉ?

**«ስልክዎን ለማየት ካልቻሉ እራሱ ስልክዎ ሊያግዝዎ ይችላል። ከእነዚህ መንገዶች ውስጥ ሦስቱ የሚከተሉት ናቸው፦»**

**ማጉላት (ነገሮችን በማያ ገጹ ላይ ማጉላት)፦**

«ማጉላት በስልክዎ ላይ ያለው ነገር ሁሉ ትልቅ ሆኖ እንዲታይ የሚያደርግ ተግባር ነው። በርካታ ሰዎች ማጉላትን የሚጠቀሙት ትንንሽ ነገሮችን ለመመልከት እንዲያግዛቸው ነው። ዝቅተኛ የማየት ችሎታ ላላቸው ሰዎች በማያ ገጹ ላይ ያለውን ነገር እንዲያዩ ያስችላቸዋል።»

«ሚካኤል በየቀኑ ዜናዎችን ለማንበብ ማጉላትን ይጠቀማል፣ ጽሑፉ ከተለመደው መጠን በሦስት እጥፍ የጎላ ከሆነ ብዙ ጽሑፍ ያላቸውን ታሪኮች ለማንበብ ቀላል ሆኖ አግኝቶታል።»

## ለምን ሊጠቀሙበት ይችላሉ?

**ስልኩ ጮክ ብሎ እንዲናገር ማድረግ፦**

«'TalkBack' ማለት ማያ ገጹን ማየት ሳያስፈልግዎ ስልክዎን ማዳመጥ ሲችሉ ነው። በስልክዎ ላይ አንድ ነገር ሲያደርጉ ያናግርዎታል እንዲሁም ምን እየተከሰተ እንዳለ ይነግርዎታል በተጨማሪም የተከሰተውን ነገር ለማሳወቅ ንዝረት ይፈጥራል።»

«አይሻ ሁልጊዜ በስልኳ ላይ ማጉላትን (ማያ ገጹ ትልቅ ሆኖ እንዲታይ ማድረግን) ትጠቀም ነበር፣ ነገር ግን ከጥቂት ሰዓታት በኋላ ዓይኖቿን እንደሚያደክም በቅርብ ጊዜ ስላወቀች፣ አሁን ይህ በሚሆንበት ጊዜ TalkBackን ትጠቀማለች።»

**ቀለሞችን እና ንፅፅሮችን መቀየር፦**

«አንዳንድ ሰዎች አንዳንድ ቀለሞችን እና ንፅፅሮችን ለማየት ይቸገራሉ፣ ይህም በማያ ገጹ ላይ ያለውን ለማንበብ አስቸጋሪ ያደርገዋል። ለአጠቃቀም ቀላል እንዲሆን ለማድረግ ስልኮች ላይ ቀለም የሚታይበትን መንገድ መቀየር ይችላሉ።»

«ቀለሟ WhatsApp ወይም ኢሜይል ስትጠቀም የምትጽፈውን በቀላሉ ለማንበብ ከፍተኛ የንጽጽር ማሳያ ቅንብሮችን ትጠቀማለች። ሁሉም ነገር ግልጽ ሲሆን ጥቂት ስህተቶችን እንደምትሰራ ተገንዝባለች።»

## እንዴት ነው የሚሰራው?

- ሰልጣኙ በስልካቸው ምን ማድረግ እንደሚፈልጉ **ይጠይቁ**።
- **አሰልጣኝ፦** የሰልጣኙ ስልክ የተቀናበረ የተደራሽነት ባህሪ እንዳለው ያረጋግጡ።

# መስማት ለሚቸገሩ ወይም ምንም መስማት ለማይችሉ ሰዎች የተደራሽነት ባህሪያት

## ይህ ምንድን ነው?

**ያብራሩ፦** «ለመስማት የሚቸገሩ ወይም ምንም መስማት የማይችሉ ሰዎች እንደማንኛውም ሰው ስልኮችን መጠቀም ይችላሉ ምክንያቱም ስልኮቹ እገዛ ማድረግ የሚችሉ ባህሪዎች አሏቸው።»

## የሚያስፈልጉዎ ቁሳቁሶች፦



Android ስልክ




የተደራሽነት
ባህሪያት ፖስተሮች

## ለምን ሊጠቀሙበት ይችላሉ?

**«ስልክዎን ሊሰሙት ካልቻሉ እራሱ ስልክዎ ሊያግዝዎ ይችላል። ከእነዚህ መንገዶች ውስጥ ሦስቱ የሚከተሉት ናቸው፦»**

**ድምጽ መጨመር፦**

«በዙሪያዎ ያሉ ሰዎች የሚናገሩትን ለመስማት የሚቸገሩ ከሆነ Android ስልክዎ ሊያግዝዎ ይችላል። ድምጾችን እንዲሰሙ ግልጽ የሚያደርግ የድምጽ መጨመሪያ የሚባል ነገር አለ።»

«ተፈራ በካፌ ውስጥ ከሰዎች ጋር ሲነጋገር የድምጽ መጨመሪያ ይጠቀማል፣ ይህም የበስተጀርባ ጫጫታን ስለሚቀንስ አንድ ሰው የሚናገረውን በደንብ ለመስማት ያስችለዋል።»

# መስማት ለሚቸገሩ ወይም ምንም መስማት ለማይችሉ ሰዎች የተደራሽነት ባህሪያት

## ለምን ሊጠቀሙበት ይችላሉ?

**መግለጫ ጽሑፎች፦**

«ስልክዎ ቪድዮ ወይም ኦዲዮ በሚያጫውትበት ጊዜ መግለጫ ጽሑፎችን ማብራት ይችላሉ። ይህ ማለት እየተባለ ያለውን ቃል በማያ ገጹ ላይ ማየት ይችላሉ ማለት ነው። ይህ ሰዎች አንድን ዘፈን ወይም ቪድዮ ለመስማት ሲቸገሩ በጣም ጠቃሚ ነው።»

«ሰናይት በቪድዮ ጥሪዎች ውስጥ መግለጫ ጽሑፎችን ትጠቀማለች። አብዛኛውን ጊዜ ቃላቱን ለመስማት ስትቸገር መግለጫ ጽሑፎቹ ለጥሪው ትኩረት እንድትሰጥ እንደሚያግዟት ትገነዘባለች።»

**ግልባጭ ጽሑፍ፦**

«የቀጥታ ስርጭት ግልባጭ ጽሑፍ ከመግለጫ ጽሑፎች ጋር ተመሳሳይ ናቸው። ይህም ሰዎች በሚናገሩበት ጊዜ የሚናገሩትን ነገር በማያ ገጹ ላይ በጽሁፍ ማየት ይችላሉ ማለት ነው። ትንሽ ለሚሰሙ ወይም ምንም መስማት ለማይችሉ ሰዎች የቀጥታ ስርጭት ግልባጭ ጽሑፍ በጣም ጠቃሚ ሊሆን ይችላል።»

«አህመድ የጆሮ ማዳመጫውን ከስልኩ ጋር ያገናኘዋል፣ ይህም በWhatsApp በኩል ከወንድሙ እና ከእህቱ ጋር ሲነጋገር ንግግርን የበለጠ ግልጽ እና ለመረዳት ቀላል ያደርገለታል።»

**ለሰልጣኙ ጠቃሚ** እንዲሆን ያድርጉት፦ እነዚህ ባህሪያት እንዴት በሰልጣኙ ህይወት ውስጥ ጠቃሚ ሊሆኑ እንደሚችሉ ይወያዩ።

## እንዴት ነው የሚሰራው?

- ሰልጣኙ በስልካቸው ምን ማድረግ እንደሚፈልጉ **ይጠይቁ**።
- **አሰልጣኝ፦** የሰልጣኙ ስልክ የተቀናበረ የተደራሽነት ባህሪ እንዳለው ያረጋግጡ።

# ፖስተሮች እና ተቆርጠው የወጡ ማሳያዎች

**የስልክ በይነመረብ ክህሎቶች የሥልጠና መርጃ ስብስብ**

ሰዎችን መደበኛ የስልክ በይነመረብ ክህሎቶችን ለማስተማር የተዘጋጀ መመሪያ

# በመስመር ላይ ደህንነትዎን ለመጠበቅ ምርጥ ጠቃሚ ምክሮች

**በይነመረብ በዓለም ዙሪያ ላሉ ሰዎች ሁሉ ክፍት መሆኑን ያስታውሱ፣ ስለዚህ እንደ እውነተኛው የህዝብ መገናኛ ቦታ (ለምሳሌ፣ የገበያ ቦታ) ማየቱ አስፈላጊ ነው እንዲሁም ራስዎን በመጠበቅ እና በመስመር ላይ ለሚያደርጉት ነገር ኃላፊነት በመውሰድ ደህንነትዎን ይጠብቁ።**

## በመስመር ላይ የሚመለከቱት ነገር ሁሉ እውነት እንዳልሆነ ያስታውሱ

ማንኛውም ሰው ማንኛውንም ነገር በመስመር ላይ መለጠፍ ይችላል፣ ስለዚህ የሚመለከቱትን ሁሉ አይመኑ። ከሚያምኑት ሰው እንኳን ቢሆን እውነት ላይሆን ይችላል። መረጃን ለሌሎች ከማጋራትዎ በፊት ጥንቃቄ ያድርጉ።

## በመስመር ላይ ለተዋወቁት ሰው ገንዘብ ከመላክዎ በፊት ደግመው ያስቡ

ያልጠየቋቸውን ኢሜይሎች፣ መልዕክቶች ወይም ብቅ-ባዮች በተለይም ገንዘብ የሚጠይቁ ከሆኑ ወይም እንግዳ የሆኑ አገናኞችን ከያዙ ይጠንቀቋቸው።

## የይለፍ ቃሎችን ጨምሮ የግል መረጃዎን ለግልዎ ያቆዩ

በጣም አስፈላጊ ካልሆነ በቀር፣ እንደ ሙሉ ስምዎ፣ የቤት አድራሻዎ ወይም ስልክ ቁጥርዎ ያሉ የግል ዝርዝሮች ማጋራት የለብዎትም።

## በመስመር ላይ በሚገኙ ሌሎች ሰዎች ላይ ጉዳት አያድርሱ

መልካምነትን እና አክብሮትን ያሳዩ። ጉልበተኝነት አያሳዩ፣ የውሸት መረጃን አያሰራጩ ወይም ማንም ሰው ላይ ትንኮሳ አያድርሱ። በመስመር ላይ የሚወስዷቸው እርምጃዎች በእውነተኛ ሕይወት ላይ ያሉ ሰዎች ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድሩ ይችላሉ።

## ማጭበርበሮችን እና አጭበርባሪዎችን ይወቁ

ልክ በእውነተኛ ሕይወት እንዳለው ሁሉ፣ በበይነመረብ ላይም ሌቦች እና ወንጀለኞች አሉ። አንዳንድ ሰዎች በመስመር ላይ ሌላ ሰው እንደሆኑ ያስመስላሉ።

## የሚያስቸግርዎትን ሰው በማገድ ወይም ችላ በማለት እርምጃ ይውሰዱ

የሆነ ሰው በመስመር ላይ ካስቸገረዎ ወይም ትንኮሳ ካደረሰብዎ፣ እርዳታ ይጠይቁ እንዲሁም ለሆነ ሰው ይናገሩ ወይም ሪፖርት ያድርጉ።

# የዳታ ወጪዎች



የተደራሽነት ባህሪያት

# ዝቅተኛ ዕይታ ላላቸው ሰዎች ማጉላት



# የተደራሽነት ባህሪያት

# ጊዜያዊ ማጉላት



የተደራሽነት ባህሪያት

# TalkBack ማቀናበር



የተደራሽነት ባህሪያት

# ድምፅ ማሻሻያ



# የተደራሽነት ባህሪያት

# ድምፅ መጨመር

## 1




## 2




## 3




## 4



የተደራሽነት ባህሪያት

# መግለጫ ጽሑፎችን ማቀናበር



